ቁጥር ፈ/1162/11/764
ቀን ጥቅምት 22 2015

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

ለጉሙዝ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ጉሕዴን)

አሶሳ፤

ጉዳዩ፡ ቀደም ሲል በቦርዱ የተወሰነውን የፓርቲውን የፍቃድ ስረዛን ይመለከታል፤

የጉሙዝ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ጉሕዴን) በአዋጁ 1162/2011 እና በቦርዱ በወጣው መመሪያ ቁጥር 3 መሠረት ጠቅላላ ጉባዔ በማድረግ በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ ማሻሻያ አድርጎ በዳግም ምዝገባ ሂደት ውስጥ ማለፍ ካለባቸው ፓርቲዎች መካከል በመሆኑ ይህንኑ እንዲፈጽም ከቦርዱ መመሪያ ተሰጠው፡፡

በዚሁ መሠረት ፓርቲው ጉባዔ አድርጎ ሪፖርት ለቦርዱ አቅርቦ ነበር፤ ቦርዱም በወቅቱ የቀረበለትን ሪፖርት ከሕጉና ከመመሪያው አንፃር በመመርመር ያልተሟሉ ዝርዝር ጉዳዮችን እንዲያሟላ ለፓርቲው አስታወቀ፡፡ ይሁንና ፓርቲው በወቅቱ ማሟላት የሚገባውን ባለማሟላቱ ከምዝገባ እንዲሰረዝ ቦርዱ ወሰነ፡፡

ሆኖም ፓርቲው በወቅቱ የተጠየቀውን ሊያሟላ ያልቻለው የፓርቲው አመራሮች በሙሉ በእስር ቤት በመሆናቸው ምክንያት መሆኑን፤ አሁን ከረዥም እስር በኋላ አመራሮቹ እና አብዛኛው አባላት ከእስር እንደተፈቱ፤ እንዲሁም ቦርዱ ከዚህ በፊት ፓርቲው እንዲያሟላ የጠየቀውን መፈፀም የሚችልበት ሁኔታ ላይ አሁን እንደሚገኝ በመግለጽ የፓርቲውን ፈቃድ ስረዛ እንዲነሳለት ጥቅምት 1 እና ጥቅምት 18 ቀን 2015 ዓ.ም. በፃፋቸው ሁለት ደብዳቤዎች ቦርዱን ጠይቋል፡፡

ለድምጽዎ የሚያምኑን

አድራሻ - ቦሌ ክፍለሚገን
ሪስቶራንት ገባ ብሎ በስተቀኝ
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
ስልክ +251 115 153468
ፋክስ +251 115 510025
ፌስቡክ /national-electoal-board-of-ethiopia-nebe
ትዊተር @NEBEthiopia
ኢሜይል contact@nebe.org.et
ድረ - ገጽ www.nebe.org.et

ቦርዱ ይህን የቀረበለትን አቤቱታ ጥቅምት 21 ቀን 2015 ዓ.ም. ባደረገው ስብሰባ መርምሮ ያልተሟሉ ጉዳዮችን ፓርቲው አሟልቶ እንዲያቀርብ በጠየቀበት ወቅት አመራሮቹ በሙሉ እንዲሁም አባላቱ በእስር ላይ መሆናቸውን ከቀረቡለት ሰነዶች አረጋግጧል፡፡ በዚሁ መሠረት በወቅቱ የተጠየቀውን ያላሟላው ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ገጥሞት መሆኑን በመገንዘብ ቦርዱ ታህሣሥ 30 ቀን 2013 ዓ.ም. ባካሄደው ስብሰባ በፓርቲው ላይ የሰጠውን የመሰረዝ ውሳኔ እንዲነሳ ወስኗል፡፡

በመሆኑም ፓርቲው ከዛሬ ጥቅምት 21 ቀን 2015 ዓ.ም. ጀምሮ ሕጋዊ ሰውነት ያለው ፓርቲ ሆኗል፡፡ ይህ ውሳኔ ከተሰጠበት ከዛሬ ጥቅምት 21/2015 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ጥር 21/2015 ዓ.ም. ባሉት (ሦስት ወራት) ጊዜያት ውስጥ ጠቅላላ ጉባዔ በማድረግ ከዚህ በፊት ለፓርቲው መሰረዝ ምክንያት የሆኑትን ሁሉ በማስተካከል እንዲያቀርብ በአክብሮት እናሳውቃለን፡፡

ከበጎምኞት ጋር

ብርቱካን ሚደቅሳ
የኢትዮጵያ ብሔራዊ
ምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ